በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዚያ 2015

<u>አዲስ አበባ</u>

ማውጫ

		ገፅ
ክፍል አንድ	መግቢያ	
1.1.	የጥናቱ ዳራ	
1.2.	የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት	
1.3.	የጥናቱ ዓላማ	
ክፍል ሁለት	በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ	
ክፍል ሶስት	የጥናቱ ስነ-ዘዴ	
3.1.	የጥናቱ ወሰን	
3.2.	የዝግጅት ምዕራፍ	
3.3.	የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች	
3.4.	የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ	
3.5.	የጥናቱ ተግዳሮቶች	
3.6.	የጥናቱ ውስንነቶች	
ክፍል አራት	ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና	
4.1.	የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት	
4.2.	ተጠያቂነትን ማስፈን	
4.3.	የተቋማት ግልጽነት	
4.4.	አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ	
4.5.	የንብረት አስተዳደር	
4.6.	የግዥ አስተዳደር	
4.7.	የሰው ሃብት አስተዳደር	
4.8.	የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ	
4.9.	የፕሮጀክቶች አስተዳደር	
4.10.	ኦዲትና ቁጥጥር	
4.11.	የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና	
ክፍል አምስት	ምክረ-ሀሳቦች	
	ማጣቀሻ ፅሁፎች	

ክፍል አንድ፦ መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው ወንጀል ሲሆን፤ በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትል ችግር ነው፡፡ ሌላው ሙስና በአደራ የተሠጠን ኃላፊነት ለግል ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ማስገኛ መሣሪያ አድርጎ መጠቀም ነው፡፡ የሙስና መንሠራፋት የህግ የበላይነትን ያጣምማል፣ የኢኮኖሚ እድገትን ያቀጭጫል፣ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን ያዳክማል፣ የኢንቨስትመንት ፍሰት ይገታል እንዲሁም ሥርዓት አልበኝነት እንዲንሰራፋ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ አገሮች ፣ ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ስጋቶች መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ የሙስና ስጋቶችን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን የአደጋ መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል፡፡ እንደዚህ አይነት እርምጃዎች የመንግስት እና/ወይም የግሉ ሴክተር ድርጅቶች ጥረታቸውን እና ሀብታቸውን በጣም አንገብጋቢ እና ተፅእኖ በሚፈጥሩ የትኩረት ቦታዎች ላይ እንዲያውሉ ያስችላቸዋል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ ዓመታት አስፈላጊ ህጎች እንዲወጡ በማድረግ እና በመተግበር ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናትና ምርምር በማድረግ ሙስናን መከላከል አንዱ ነው፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጀቶችና አሰራሮች በዘርፍ ደረጃ ሲተገበሩ የሙስና ሥጋት ተጋላጭነታቸውን በየወቅቱ በመለየት ወቅታዊ መፍትሔ የመስጠት ሥራ በቂ ትኩረት ተሰጥቶታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ኮሚሽኑ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ሥራን በተቋም ደረጃ የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲደራጁ በማድረግ ወደ ተግባር ቢገባም፣ እስካሁን በተቋማቱ ውስጥ የሙስና መከላከል ተግባራት የተገኘዉ ዉጤት በሚጠበቀው ደረጃ ላይ ደርሶ አልተገኘም፡፡

በዘርፉ ስር ሊከሰቱ የሚችሉ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራርብ፤ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር እና የመረጃ አያያዝ ጥራት ችግር ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሠራሮች እንደሆኑ ይጠቀሳል፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ክስተቶች በተለያዩ ዘርፎች ስር ባሉ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከያ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

1.2. የዘርፉ ተቋማት ሥልጣንና ተግባራት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 39 መሰረት ለውጭ ጉዳይ ዘርፍ (ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት) ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ሀገሪቱ ባላት የውጭ ግንኙነት ጥቅሟና መብቷ እንዲጠበቅና በሌሎች መንግሥታት እንዲከበር ያደርጋል፤ ሀገሪቱ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤
- ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ዓለም አቀፍ ውሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይደራደራል፣ ይፈርማል፤ ዓለም አቀፍ ውሎች እንዲጸድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ዓለም አቀፍ ውሎች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
- የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በማካሄድ የሀገሪቱን የውጭ ንግድና ቱሪዝም ለማስፋፋት፣ የውጭ ኢንቨስተሮችን ለመለየትና ለመሳብ፣ ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት፣ የውጭ የልማት ፋይናንስና የቴክኒክ ተራድኦ የሚገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ ለሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ድጋፍ ይሠጣል፤ እንዲሁም በፐብሊክ ዲፕሎማሲና ኮሙኒኬሽን ተግባራት የሀገር ገጽታን የመገንባትና ደጋፊዎችን የማበራከት ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
- በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ በኢትዮጵያውያን ማህበረሰብና በኢትዮጵያ ወዳጆች የተመሠረቱ ማህበራትን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የዳያስፖራ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤ በፕሮቶኮል ጉዳዮች ላይ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
- ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ ሀገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤
- በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ ሀገራት መንግሥታት እንደራሴዎች፣ ቆንስሎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎች ለውጭ ሀገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፤

- በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚስዮኖችን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል፤
- አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ ፓስፖርቶች እና የዲፕሎማቲክና ሰርቪስ መግቢያ ቪዛዎች ይሰጣል፤

1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

አጠቃላይ ዓላማ፦

የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ተቋማትን የአሰራር ስርዓት ከሙስና ስጋት አንፃር በመገምገም የሙስና ተጋላጭነት ትንተና ማካሄድ ነው::

ንዑስ አላማዎች፦

የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ተቋማትን፥

- የአሠራር ስርዓቶች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

ክፍል ሁለት፦ በውጭ ጉዳይ ዘርፍ የሙስና ስጋት ተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

ሙስና በተደጋጋሚ 'ካንሰር' ተብሎ ይገለጻል:: የህብረተሰቡን እድገትና ደህንነት የሚያዳክም ነገር ግን ሆን ተብሎ ሌሎች ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ያልተወጠነ ክፉ ሃይል ነው:: በብዙ ሁኔታዎች ይህ ትክክለኛ መግለጫ ሲሆን በሌሎች ግን ሙሉውን ታሪክ አይገልጽም:: ይህ በተለይ ሙስናን አውቆና ሆን ተብሎ እንደ መንግሥት መሣሪያነት የውጭ ፖሊሲ ግቦችን ለማሳካት የሚረዳበት ሁኔታ ነው:: ለምሳሌ 'የአዘርባይጃኒ ላውንድሮማት' ('Azerbaijani Laundromat') ተብሎ የሚጠራውና በአጠቃላይ 2.9 ቢሊዮን ዶላር ከአዘርባጃን ኩባንያዎች እና የመንግስት መምሪያዎች በእንግሊዝ ላሉ አራት የሼል ኩባንያዎች የተላለፈ የገንዘብ ዝውውር የሀገሪቱን ዓለም አቀፍ ስም (ዝና) ለማሻሻል ባለመ መልኩ ለግል ማበልጸጊያ እና የውጭ ፖሊሲ እቅዶችን ፋይናንስ ለማድረግ ውሏል (OCCRP, 2017)::

ሌላው ደግሞ በአገሮች ኢኮኖሚያዊ እና ስትራቴጂካዊ ጥገኝነት (ለምሳሌ ወሳኝ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች፣ ዕዳ፣ ወዘተ) ላይ ተሞርኩዞ ሙስናን እንደ የውጭ ፖሊሲ መሳሪያ መጠቀም ነው:: ለምሳሌ ሩሲያ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ የዩክሬንን የሀገር ውስጥ እና የውጭ ፖሊሲ ውሳኔዎችን ለመቅረፅ ያደረገችው ሙከራ በኤነርጂ ሴክተር ውስጥ ብልሹ እቅዶችን በመጠቀም ነበር:: ሙስናን እንደ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መጠቀሚያ ማድረግ አገሮች ልማትንና ዲሞክራሲያዊ ማሻሻያዎችን የማስፋፋት ዕድሎችን ይነጠቃቸዋል:: የመንግስት ተቋማትን የህዝብ ሃብትን ወደ ግል

ኪስ ወደሚያዘዋውሩ ኔትወርኮች መልሶ በማደራጀት ጥቅም ላይ ያውላቸዋል፡፡ አምባገነን መንግስታትን ለማጠናከር እና ዲሞክራሲያዊ ስርአቶችን (ከምርጫ ማሻሻያ (reform) እስከ ጠንካራ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች) የሚያራምዱትን ለማዳከም ይጠቅማል (Transparency International, 2019)፡፡

የውጭ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ መሣሪያ አካል ሆኖ የሚዘረጋውን የሙስና አስከፊ ተጽዕኖ ለመከላከል የመጀመሪያው እርምጃ አሠራሩን በጥልቀት መረዳት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ እነዚህን ተጽዕኖዎች ሊያሳድሩ የሚችሉትን ስልታዊ ጥገኝነት መቀነስ ነው (Transparency International, 2019)፡፡

ሌላው በጣም አሳሳቢ የሆነው ጉዳይ የትላልቅ ፋይናንስ ቻናሎች በዓለም ዙሪያ ካሉ offshore (tax) havens ጋር መጣበቅ ነው፡፡ እነዚህ የንግድ ግንኙነቶች በፋይናንስ ሚስጥራዊነት፣ በቀላል (light) የፋይናንስ ደንብ እና በዝቅተኛ የኮርፖሬት ታክሶች ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ መንግስታት በህግ ላይ የተመሰረተ የውጭ ፖሊሲ እንዲከተሉ ከተፈለገ እነዚህ offshore havens በሰፊው ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸውን ሚና በሚገመግሙበት ወቅት ህጋዊ እና ህገ-ወጥ ድንበር ተሻጋሪ የፋይናንስ እንቅስቃሴን ለመለየት አዳዲስ መንገዶችን መፈለግ ይኖርባቸዋል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች ያለው የገንዘብ ፍሰት ሙስናን በእጅጉ የሚያመቻች መሆኑንም ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው (IMF, 2019).

ክፍል ሶስት፡- የጥናቱ ስነ-ዘዴ

3.1. የጥናቱ ወሰን (Scope of the study)

ይህ ጥናት የተካሄደው በፌደራል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተጠሪ በሆኑ ሁለት ተቋማት (የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት) ላይ ነው፡፡

3.2. የዝግጅት ምዕራፍ

በመጀመሪያ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 10 የትኩረት ርእሰ-ጉዳዮችን በመለየት የመረጃ መሰብሰቢያ ቼክ-ሊስት ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ 10 ርእሰ-ጉዳዮች ማንኛውም የመንግስት ተቋም ሊተገብራቸው የሚገቡና ተመሳሳይ ባሕሪ ያላቸው አሰራሮች ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው ተቋማት ከተቋቋሙበት ዐላማ አንፃር የራሳቸው የሆነ ልዩ ባሕሪ አላቸው፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ ከተቋማቱ ልዩ ባሕሪ ሊመነጩ የሚችሉና የመለያየት ሁኔታ የሚስተዋልባቸውን የሙስና ስጋቶች ለመለየት አንድ ተጨማሪ ርእሰ-ጉዳይ ተካቷል፡፡

በመቀጠልም በተዘጋጀው ቼክ-ሊስት ዙርያ ለጥናት ቡድን አባላት (መረጃ ሰብሳቢዎች) ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎች ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎችን እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ ፈጥረዋል፡፡

3.3. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ቼክ-ሊስት (የዳሰሳ መጠይቅ) እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው፡፡ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡
ቼክ-ሊስት፡- የጥናት ቡድን አባላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈላጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይህን ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሊስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ የተቋማት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ የተሞረኮዘ የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ነው፡፡

ሰነዶች፡- የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል፡
፡

የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት፡- ከ10ሩ ርዕሰ-ጉዳዮች ጋር ታያያዥነት ያላቸውን ወይም በቀጥታ በቼክ-ሊስት ውስጥ ያላተካተቱትን የሙስና ስጋቶች በጥቂቱ ለመዳሰስ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ሃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል፡፡

3.4. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው፡፡ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን (የፕሮጀክቶች የወጪ መረጃና አፈፃፀም፣ የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎች፣ የውጭ እና የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝቶች፣ ወዘተ) ለመተንተን ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች (ቼክ-ሊስት፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ተጠቅሟል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ቡድን መሪዎች አስተባባሪነት የጥናት ቡድን አባላት ከየተቋማቱ የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች በዘርፍ ደረጃ በማጠቃለል ትንተና አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ አማካሪዎች በበኩላቸው የሙስና ስጋቶችን በመለየትና በመተንተን ዘርፍ-ተኮር የሙስና መከላከል ምክረ-ሀሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡

3.5. የጥናቱ ተግዳሮቶች (Challenges of the study)

ጥናቱ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡-

- መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት የተወሰኑ የተቋማት ኃላፊዎች/ባለሙያዎች ቀጠሮ አለማክበር እና የጥናት ቡድን አባላትን ማመላለስ፣

- በአንዳንድ ተቋማት የሚፈለገውን መረጃ በወቅቱ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆንና መረጃ መከልከል፣

3.6. የጥናቱ ውስንነቶች (Limitations of the study)

ይህ የዳሰሳ ጥናት ቀድሞ በተመረጡና ለሁሉም ተቋማት ተመሳሳይ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በማተኮር የተሰራ ከመሆኑ አንፃር የዘርፉን የሙስና ስጋቶች ሙሉ ለሙሉ ለይቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ በሌላ አገላለፅ በዚህ ጥናት ያልተለዩ ሌሎች የሙስና ስጋቶች በዘርፉ ውስጥ እንዳሉ ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን በቀጣይ ለሚሰሩ ጥልቅ ጥናቶች እንደ መንደርደሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል መናገር ይቻላል፡፡

ክፍል አራት፦ ዘርፍ-ተኮር የሙስና ስጋት ትንተና

የውጭ ጉዳይ ዘርፍ የስራ አፈጻጸም እና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ትንተና በ11 ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የቅንነት፣ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ዋና እሴቶች ላይ የተመሰረተ ሥነምግባራዊ ድርጅታዊ ባህልን ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ክፍሎቹ ከተሰጣቸው ኃላፊነቶች መካከል፣ የክልል እና የፌደራል ህጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የተቋሙን የሥነምግባር ፖሊሲዎች መገምገም እና ማዘመን፣ በተቋሙ ውስጥ ካሉ የስነምግባር ጉዳዮች ጋር በተያያዙ የህግ መስፈርቶች ላይ ከፍተኛ አመራሮችን ማማከር፣ ለአመራር እና ሰራተኞች በሥነምግባር ደረጃዎች (ethical standards) ላይ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት እና መተግበር እንዲሁም የሰራተኞች የሥነምግባር ጉድለትን በተመለከተ የሚነሱ ቅሬታዎችን መገምገም እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መምከር ይገኙበታል፡፡ የሥነምግባር ክፍሎች እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት በሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በቁሳቁስ፣ ወዘተ መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

የውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር የሚገኙ ሶስቱም ተቋማት በተፈቀደው የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ መደብ በሰው ኃይል እንዲሟላ እንዳላደረጉ ከቅጥር ደብዳቤዎች እና ከተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይ በአንዱ ተቋም አንድ ባለሙያ ብቻ በውክልና ከሌሎች ስራዎች ጋር በተደራቢነት ይዞ እንዲሰራ መደረጉን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አመታዊ ዕቅድ አላቸው፡፡ ምቹ የስራ ቦታ ከመፍጠር አንፃር፣ በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ሶስት ተቋማት ውስጥ ሁለቱ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ሟሟላታቸው በበጎ ጎን የሚታይ ሲሆን ቀሪው አንድ ተቋም ግን በተደራቢነት የሚሰራ እንደመሆኑ መጠን የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ የራሱ ቢሮ የሌለው መሆኑን በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በጀትን በሚመለከት በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ አንዱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ የራሱ በጀት የተመደበለት ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ሁለቱ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን የራሳቸው

በጀት ያልተመደበላቸው ቢሆንም ስራዎቻቸውን ሲያቀርቡ በፑል ከተያዘ በጀት የሚፈቀድበት አሰራር እንዳለ ለማየት ተችሏል፡፡

በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ከሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተጨማሪ የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ የግዢ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪም ከአንዱ ተቋም በስተቀር በሌሎቹ ሁለት ተቋማት ውስጥ የህግ ክፍል ተደራጅቷል፡፡

በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ሁለቱ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ ጥቆማ የሚሰጥበት የሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ኢ-ሜይል፣ ድረ-ገጽ እና ስልክ የመሳሰሉት ዘመናዊና ተደራሽ የጥቆማ መስጫ መንገዶች የተገበሩ ሲሆን በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ግን የጥቆማ መቀበያ ስርዓት አለመዘርጋቱ በምልከታ ተረጋግጧል፡፡ በዘርፉ ስር የሚገኙ ሁለት ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች (ከህግ ክፍል፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር ግን በስነምግባር መከታተያ ክፍል እና በኢንስፔክሽን የስራ ክፍሎች በቅንጅት የተካሄዱ የማጣራት ስራዎች እንዳሉ በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

የሕግ ክፍል ራሱን ችሎ ከተቋቋመባቸው ሁለት ተቋማት መካከል በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተለያዩ የኪራይ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት አስተያየት የሚሰጥበት አሠራር ስርዓት ያለ ቢሆንም፤ የግንባታ ስራዎች፣ የግዥ እና ሌሎች ውሎች ላይ ግን የህግ ክፍሉ አስተያየት የሰጠባቸው ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የህግ ባለሙያ ምንም አይነት ውሎች ላይ አስተያየት እንዳልሰጠ ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በቀሪው አንድ ተቋም ግን የህግ ክፍል ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ውሎች ላይ አስተያየት የሚሰጥበት አሰራር እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡
፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በሁሉም የዘርፉ ተቋማት የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በሰው ኃይል አለመሟላታቸው የሙስና ስጋት ግምገማ በማካሄድ አደጋን መሰረት ያደረገ የሙስና መከላከል ስልት ለመንደፍና የቁጥጥር ስርአትን ለማዳበር የሚያስችል አደረጃጀት እንደሌላቸው ጠቋሚ ነው፡፡ በተለይ የአንዱ ተቋም የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተደራቢነት የሚሰራና የራሱ ቢሮ የሌለው መሆኑ የተቋሙ አመራር ሥነምግባርን በማስረፅ ረገድ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በቸልተኝነት ወደጎን እንደተወ አመላካች ነው፡፡
- በአንዱ የዘርፍ ተቋም የጥቆማ ስርአት አለመዘርጋቱ የታለሙ/የታቀዱ ወይም በስውር የሚፈጸሙ ብልሹ አሰራሮች ወደ ወንጀል አድገው ጉዳት ሳያደርሱ አስቸኳይ የማጣራት ሥራ በማከናወን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በዘርፉ ሥር ከሚገኙ ተቋማት በአብዛኛው ይህን ስርዓት መዘርጋታቸው ግን የሚበረታታ ነው፡፡
- ብልሹ አሰራሮች ሲከሰቱ አጣርቶ ተጠርጣሪዎችን ለህግ የሚያቀርብ እና ተዛማች ስራዎችን የሚሰራ ራሱን የቻለ የህግ ክፍል አለመኖር ለሙስና በር ሊከፍት ይችላል፡፡

- የአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ከሌሎች ክፍሎች ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም። ይህ ግኝት ቅንጅታዊ አሰራር መደበኛ እና የተዋቀረ (structured) የሙስናና ብልሹ አሰራር መረጃ ልውውጥ ለማድረግ እንዲሁም የጋራ ትንተና ለማካሄድ ካለው ፋይዳ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን አለማድረጋቸውን አመላካች ነው።
- በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በህግ ክፍል አስተያየት እንዲሰጥበት የሚደረግበት አሠራር ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ መደበኛ አሰራርን ችላ በማለት እንዲሁም ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ውሎች ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው።

4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

የተጠያቂነት ስርአት የተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊታቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበት የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው። የዚህ ስርአት በአግባቡ ተግባር ላይ መዋል ማንኛውም አመራር/ሰራተኛ ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት አንፃር በአፈፃፀሙ፣ በውሳኔውና በሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች እንደሚገመገም እንዲሁም ብልሹ አሰራሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ እንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ማረጋገጫ ይሰጣል። ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ተጠያቂነትን ከማስፈን ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር የሚገኙ ሶስቱም ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች አሰራርን በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ያካሄዱ ቢሆንም በጥናቱ መሰረት ማሻሻያዎች ስለመደረጋቸው መረጃ አልቀረበም። ይህም ለሙስና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ አሰራሮችን በጥናት በመለየት የተሰጡ ምክረ ሃሳቦችን ተግባራዊ በማድረግ ግልጽነትና ተጠያቂነት ከመፍጠር አኳያ በቀጣይ ትኩርት ተሰጥቶ መሰራት እንዳለበት አመላካች ነው። በተጨማሪም በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የደንበኞች እርካታ በየጊዜው በገለልተኛ አካል የሚጠና ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም።

ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ነው። ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የሆነው የውጭ ጉዳይ ሚ/ር የፀደቀ የሥነምግባር ደንብ ሲኖረው፣ የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ደግሞ በረቂቅ ደረጃ አዘጋጅቷል። የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ግን የስነምግባር ደንብ ስለማዘጋጀቱ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም። በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር የሚገኙ ሶስቱም ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎች እንደሰሩ ቢገልጹም፤ የተሰሩ ስራዎችን የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም። በተጨማሪም የሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ ክንውን ሪፖርት ለተቋማቱ የበላይ አመራሮች የሚላክ መሆኑን

ከተሰበሰቡ መረጃዎች ማረጋገጥ ቢቻልም፣ የበላይ አመራሮች የሰጡትን ግብረ-መልስ የሚያሳይ መረጃ ግን አልቀረበም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ሁሉም የዘርፉ ተቋማት የሙስና ስጋት ጥናት ማካሄዳቸው የሚያበረታታ ቢሆንም በጥናቱ መሰረት ማሻሻያዎች አለመደረጋቸው ጥናቱን ፍሬ-አልባ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ተቋማት የደንበኞች እርካታን በየጊዜው በገለልተኛ አካል አለማስጠናታቸው ከደንበኞች የሚነሱ ለሙስና ሊያጋልጡ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮችን በመመርኮዝ ቅድመ-መከላከል ስትራተጂዎችን ለመቅረፅና የተጠያቂነት ስርዓትን በሚፈለገው መጠን ለመዘርጋት የሚያስችላቸውን ዕድል/አጋጣሚ ያሳጣቸዋል፡፡
- አብዛኞቹ የዘርፉ ተቋማት የፀደቀ የሥነምግባር ደንብ የላቸውም፡፡ የደንቡ አለመኖር የተቋማቱን እሴቶች፣ ደንቦች፣ ደረጃዎች እና መርሆዎች በተመለከተ አመራርና ሠራተኞች በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው በማድረግ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን መሰረት አድርጎ ሥራን ከመስራት አኳያ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡
- በዘርፉ ስር የሚገኙ የሁሉም ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የስራ ክንውን ሪፖርታቸውን ለበላይ አመራሮች የሚልኩ ቢሆንም፣ የበላይ አመራሮች የሰጡትን ግብረ-መልስ የሚያሳይ መረጃ ግን አልቀረበም፡፡ ይህም የተቋማት አመራሮች በተቋማቸው ለሚካሄድ የፀረ-ሙስና ትግል የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ላይ ክፍተት እንዳለ አመላካች ነው፡፡
- በዘርፉ ስር የሚገኙ ሶስቱም ተቋማት የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ-መከላከል ስራዎችን የሚያሳይ መረጃ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም የሙስና ስጋቶች አድገው ወደ ሙስና ከመሸጋገራቸው በፊት በመረጃዎች ላይ በመመስረት የሚወሰድ የእርምት እርምጃ አለመኖር ለሃብት ብክነትና ለደንበኞች እንግልት ሊዳርግ ይችላል፡፡

4.3. የተቋማት ግልፅነት

የመንግስት ተቋማት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግልፅነትን ሊላበሱ ይገባል፡፡ ግልፅነት ዜጎች ለህብረተሰቡ አገልገሎት ለመስጠት የተዋቀሩ ተቋማትን የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮችን መንስኤ እና መዘዞችን በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያጠቃልለ ነው፡፡ ግልፅነት የጎደለው አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ምንም እንኳን መልካም ውጤት ቢመዘገብም የተአማኒነት እና ቅቡልነት ጥያቄ ሊነሳበት ስለሚችል የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ከሠራተኞችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት ወደ ተግባር እየተገባ መሆኑን ከተሰበሰበ መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም የዕቅድና በጀት ትግበራው የተሳካ እንዲሆን አጋዥ ሚናውን ይጫወታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዘርፉ

የሚገኙ አብዛኞቹ ተቋማት ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ በተቋሞቹ ውስጥ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች በውስጥ ማስታወሻ ተደራሽ የሚደረግ ሲሆን፣ ለሌሎች የውጭ ተገልጋዮች ተደራሽ የሚደረግበት አሰራር ስለመኖሩ ግን መረጃ አልቀረበም፡ ፡

በዘርፉ ስር በሚገኙ ሁሉም ተቋማት በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ በጥናቱ ወቅት ከተሰበሰበ መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች በድህረ-ገጽ፣ በብሮሽር እና በሌሎች ዘዴዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ስለመደረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የግዥና ጨረታ ማስታወቂያ በይፋ በጋዜጣ እንደሚያሰራጩ እንዲሁም ተቋማዊ መረጃ የሚሰራጩበት ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ድህረ-ገጽ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ተቋማት ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን ስለመስጠታቸው የሚያሳይ መረጃ ባይቀርብም፣ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ለሚዲያዎች መግለጫዎች እንደሚሰጥ በውይይት ወቅት ተገልጿል፡፡

ውሳኔዎች እና ቃለ-ጉባኤዎች ለውጭ ተገልጋዮች ተደራሽ አለመደረጋቸው ገንቢ አስተያየቶች የመሰብሰብ እድልን ያጠበዋል፡፡ ለመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ መሆን ላይ ያሉ ውስንነቶች መረጃዎች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዳይሆኑ በማድረግ አጠቃላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች ለህዝብ ግልጽ እንዳይሆኑ በማድረግ በነፃ ሊሰጡ ለሚገባቸው አገልግሎቶች ተገልጋዮችን ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ለመጠየቅ ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ስር ያሉ ተቋማት እነዚህ ጉዳዮች ላይ አበክረው ሊሰሩ ይገባል፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ግልፅ የበጀት ሂደትና አጠቃቀም መረጃ የሕዝብ አመለካከት እና ጥቅም እንደሚከበር እንዲሁም የመንግስት ገንዘብ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንደሚውል በህብረተሰቡ ዘንድ እምነትን ያሳድራል፡፡ ስለሆነም ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የሚደረግበት አሰራር አለመኖሩ ተቋማቱ የተመደበላቸውን ሃብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸውን በተመለከተ ጥያቄ የሚያስነሳ የግልፅነት ክፍተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡
- አብዛኛው የዘርፉ ተቋማት ለሚዲያ፣ ለምርመራ ጋዜጠኞች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን ስለመስጠታቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ ሚዲያ (በተለይም የምርመራ ጋዜጠኝነት) ሙስናን ለህዝብ እይታ በማጋለጥ እንዲሁም ያለምንም ተጠያቂነት (with impunity) የሚፈፀሙ ጎጂ ስራዎችን በመዋጋት ረገድ ከሚጫወተው ወሳኝ ሚና አንፃር ለመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ አለመሆን የሙስና ስጋት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸውን መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግን በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡ ፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት በጥናቶች እና በዕለት-ተለት ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች በመነሳት አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ እየተሰራ ስለመሆኑ፣ ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱ እንዲሁም ፀድቀው የሚወጡ ህጎችና መመሪያዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡ በተመሳሳይም የዜጎች ቻርተር በውጭ ጉዳይ ሚ/ር እንደተዘጋጀ በውይይት ወቅት ቢገለጽም በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ምንም አይነት አመላካች ሰነድ አልቀረበም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ለአመራርና ሰራተኞች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ጉዳዮች ላይ ስልጠና አለመሰጠቱ በሠራተኞች ሥራ አፈፃፀም ላይ ከሚያሳድረው አሉታዊ አስተዋጽኦ በተጨማሪ ሠራተኞች ከዕውቀት ማነስ ጋር ተያይዞ ለብልሹ አሠራር እንዲጋለጡ ክፈተት ሊፈጠር ይችላል፡፡
- የዜጎች ቻርተር አለመዘጋጀቱ በዘርፉ ስር የሚገኙ ተቋማት አሠራር ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዳይኖረው በማድረግ ለሙስናና ብልሹ አሠራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

4.5. የንብረት አስተዳደር

የንብረት አስተዳደር ስርአት ውጤታማነት የሚለካው ከንብረት ርክክብ እስከ ማስወገድ ድረስ በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ ንብረትን ከማስተዳደር አኳያ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የተገዙ ንብረቶችን መረከብ፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅ፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ያለአገልግሎት የተቀመጡትን (ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ያጨረሱትን) የንብረት አስተዳደር መመሪያን በተከተለ መልኩ ማስወገድ ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ በማካሄድ የማረጋገጥ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርአት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በሁሉም ተቋማት እየተተገበረ የሚገኘ የቢን ካርድ እና የቋሚ ንብረት ምዝገባ አጠቃቀም ስርዓትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ወደተሟላ የአውቶሜሽን ስራ IFMIS ለማስገባት ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ከንብረት አያያዝ ጋር በተያያዘ የካይዘን ንብረት አሰተዳደር ስርዓት

በሁሉም ተቋማት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይም በዘርፉ ስር በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ስለመደረጉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ የንብረት ቆጠራ መደረጉ፣ በንብረቶች ላይ የሚደረግ የቁጥጥር ስርዓትን በማጠናከር የመንግስት ንብረት አላግባብ እንዳይባክን ከማድረግ አንጻር ተቋማቱ የሄዱበት ርቀት የሚበረታታ መሆኑን ያሳያል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት በሶስቱም ተቋማት ንብረቶች በስጦታ እና በሽያጭ መልክ እንደተወገዱ በሰነድ ተረጋግጧል:: በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው (አገልግሎት የማይሰጡ) ኮሚፒውተሮች፣ ላፕቶፖች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ፕሪንተሮች እና የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች አስወጋጅ ኮሚቴ በማዋቀር ለተለያዩ ድርጅቶች በስጦታ በመስጠት እንዲወገዱ ተደርጓል:: እንዲሁም የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የተከማቹ ጋዜጦችን በግልፅ ጨረታ እንዲወገዱ አድርጓል:: በሁሉም ተቋም የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝራቸው ቀርቦ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የተወገዱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የሚወገዱ ንብረቶች ተገቢው ጥበቃ እና አያያዝ እየተደረገላቸው መሆኑን በምልከታ ተረጋግጧል፡፡

በመጠይቁ ከተቀመጡ ጉዳዮች አንፃር፣ የዘርፉ ተቋማት የንብረት አስተዳደር ስርአት በመልካም ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ጥናቱ አሳይቷል::

4.6. የግዥ አስተዳደር

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን አስፈላጊ የሚባሉ ግብአቶችንና የስራ መሳሪያዎችን ሟሟላት ይጠበቅባቸዋል:: እነዚህን ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የዕቃና የአገልግሎት ግብአቶችና መሳሪያዎች ለሟሟላት የግዥ ስርአትን የተከተለ ስልታዊ አካሄድ ይጠይቃል:: የግዥ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናቱ እንደሚከተለው ተንትኗል::

በዘርፉ ስር ያሉ ሁሉም ተቋማት ከስራ ክፍሎች በሚሰበሰብ የግዥ ፍላጎት መሰረት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ እንደሚያዘጋጁ፣ በመቀጠልም በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተገምግሞ እና ፀድቆ ወደ ግዥ ኤጀንሲ እንደሚላክ በሰነድ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግዥ አፈፃፀም ላይ ግምገማ እንደሚያከናውኑ ለማወቅ ተችሏል::

ከተገኘው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት እና በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት በ2014 በጀት ዓመት ከተከናወኑ ግዥዎች መካከል በድምሩ 6.7 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን በፕሮፎርማ የግዥ ዘዴ እንዲሁም ከ12.2 ሚሊዮን ብር በላይ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ተከናውነዋል:: በተመሳሳይ ዓመት በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ከ2.8 ሚሊዮን ብር በላይ ከዕቅድ ውጭ ግዥ ተከናውኗል:: በተጨማሪም የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከ 6.4 ሚሊዮን ብር በላይ የቀጥታ የግዥ ዘዴን በመጠቀም የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች ግዥ መፈፀሙን በ2013 የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተከናወኑ ግዥዎች በምን ዘዴዎች እንደተፈፀሙ ግን መረጃ አልቀረበም::

ግዥ ስቶክ ውስጥ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ መሆኑን በተመለከተ፣ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር የግዥ ክፍል የንብረት ቆጠራ ሪፖርትን በመጠቀም እና በማቀናነስ እንዲገዛ የተጠየቀ ንብረት ስቶክ ውስጥ መኖሩን ወይም አለመኖሩን በራሱ በማረጋገጥ ግዥ እንደሚፈፀም፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት በተቋሙ ያሉ ንብረቶች ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑና በቀላሉ ማወቅ ስለሚቻል የንብረት ክፍልን ማረጋገጫ ሳይቀርብ ግዥ እንደሚፈፀም በውይይት ወቅት ግንዛቤ ተይዟል፡፡ በአንፃሩ በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት እንዲገዛ የተጠየቀ ንብረት በቅድሚያ በስቶክ መኖሩ/ አለመኖሩ በንብረት ክፍል ማረጋገጫ እየቀረበበት ግዥ እንደሚፈፀም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም ግዥ ከመፈፀሙ በፊት ሚዛናዊ የቁጥጥር ስርዓት መኖሩን ያሳያል፡፡

በሁለት ተቋማት ግዥ ከመከናወኑ በፊት የገበያ ዋጋ መረጃ ከኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት በመጠየቅ ግዥ የሚፈፀም ሲሆን፣ የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ደግሞ የራሱን የገበያ ዋጋ ጥናት አድራጊ ኮሚቴ በማዋቀር ግዥ እንደሚፈፀም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ተቋማት የEGP ስርአትን ተግባራዊ ለማድረግ የሄዱበት ርቀት የሚያበረታታ ነው፡፡ ይህ የግዢ ስርአት ሃብትን በቁጠባ ለመጠቀምና የግዥ ሥርዓቱን በእቅድ ከመምራት አንፃር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ከ2014 የበጀት ዓመት ግዥ አፈፃፀም ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው በዘርፉ ተቋማት ቅሬታ የቀረበባቸው እንዲሁም የሙስና ጥርጣሬ ቀርቦባቸው የተሰረዙ ግዥዎች አልነበሩም፡፡ ይህ በጎ ልምድ ሊበረታታና ሊቀጥል ይገባዋል፡ ፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- በርካታ ሚሊዮን ብሮች ግምት ያላቸው ከዕቅድ ውጭ፣ በቀጥታ፣ በውስን ጨረታ እና በፕሮፎርማ የተከናወኑ ግዥዎች መኖር የዘርፉ የግዥ ስርዓት የሙስና ስጋት እንዳለበት አመላካች ናቸው፡፡
- በሁለት የዘርፉ ተቋማት ግዥ ከመፈፀሙ በፊት የሚደረግ ሚዛናዊ የቁጥጥር ስርዓት (check & balance) አለመኖሩ ለተደጋጋሚ ግዥ በማጋለጥ የመንግስት ሃብትን ለብክነት የሚያጋልጥ ከመሆኑም በተጨማሪ የተቋማቱን የስቶክ አስተዳደር ወጪ እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል፡ ፡

4.7. የሰው ሃብት አስተዳደር

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መሰረታዊ ግብአቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያላቸው የሰው ሃብት ነው፡፡ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ሃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት የቅጥር፣ የዝውውር፣ የዲሲፒሊን፣ ወዘተ ኮሚቴዎች ማደራጀታቸው፣ እንዲሁም የሰራተኛ ቅጥር ለመፈፀም ማስታወቂያዎችን በጋዜጣ ወይም በመገናኛ ብዙሀን የማስተዋወቅ ስራ እየሰሩ መሆኑን ከተቋማት የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ። የሰራተኞች ምደባና ዕድገት በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆንም ለማድረግ የሚያስችል ስርአት የተዘረጋና ሕጉን በተከተለ መልኩ እየተሰራ መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል። በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ከቅጥር፣ ዝውውር፣ ዕድገት፣ ስልጠና እና ምደባ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ስለመቅረቡ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም።

በመንግስት በኩል ከ2012 ዓ.ም በፊት ሃሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ እንዲከናወን አቅጣጫ ቢቀመጥም በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከተከናወነው ጅምር ስራ ውጪ በቀሪዎቹ ሁለቱ ተቋማት መረጃው እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ እየተሰራ አለመሆኑ መረዳት ተችሏል። በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት የስራ ኃላፊዎች ምደባ በውድድር ላይ ተመስርቶ እየተካሄደ መሆኑን ከሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል። በአንፃሩ በተቋማቱ ውስጥ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት መረጃ ስርዓት የማደራጀት ጅምር ስራዎች እንዳሉ ቢገለፅም መረጃውን ማግኘት አልተቻለም። ስልጠናን በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ለአመራርና ሰራተኞች በተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የስነምግባርና የሙያ ማጎልበቻ ስልጠናዎችን ሰጥተዋል።

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ አለመስራታቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። የሰነድ ማጭበርበር እንደ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም አገልግሎቶች ያሉ ጥቅማጥቅሞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ለማግኘት በማሰብ ሆን ተብሎ የሚደረግ አታላይ ድርጊት ከመሆኑ አንፃር የማጣራት ስራ አለመሰራቱ ተቋማቱን ለከፍተኛ አደጋ ሊያጋልጣቸው ይችላል።
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሰው ሃብት አስተዳደር ስርአት በዘርፉ ተቋማት አለመገንባቱ በቅጥር፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ወዘተ ውሳኔዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል።

4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሃብት ምዝገባ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተቋማዊ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይጋጩ በራሳቸው መንገድ እንዲመሩ ለማድረግ፣ አላግባብ የተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትን ለማጋለጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ጥልቅ ፋይዳ ያለው ሥርዓት ነው። ሥርዓቱ በተባበሩት መንግስታት የፀረሙስና ስምምነት፣ በአፍሪካ ህብረት የሙስና መዋጊያ እና መከላከያ ስምምንት እንዲሁም የዓለም

አቀፍና የአህጉር አቀፍ የፀረሙስና ስምምነቶችን ተቀብለው በሚፈፅሙ ሀገራት እየተተገበረ ይገኛል፡ ፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ሥርዓቱን ባለፉት አሥር ዓመታት ስትተገብር ቆይታለች፡፡ ሃብትና የገቢ ምንጫቸውን ማስመዝገብ ካለባቸው አካላት መካከል የፌደራል ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት እና በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የሃብት ምዝገባ ማድረግ የሚገባቸው አመራሮችና ሰራተኞች በሙሉ በህጉ መሰረት ሀብታቸውን አስመዝገበዋል፡፡ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር ካሉት ከ1400 በላይ አመራርና ሰራተኞች ውስጥ ሀብታቸውን ያስመዘገቡት 171 ብቻ መሆናቸው በተሟላ መልኩ የሃብት ምዝገባ ስራ አለመከናወኑን ያመላክታል፡፡ ይህም የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና ምንጫቸው ያልታወቀ ሀብቶችን ለመለየት ካለው ፋይዳ አንፃር እንደስጋት ምንጭ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜያቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ህጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ቴክኒካል ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የተለየ የኦዲት መዋቅር ባለመኖሩ፤ በተለያዩ አካላት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለጥራት መጓደልና ብክነት እየተጋለጡ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክትን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ፣ በጀትና የጥራት ደረጃ ለማጠናቀቅ የዲዛይን ጥራት፣ የጨረታ አወጣጥ ሂደት፣ የክፍያ ስርአት፣ የኮንትራት አስተዳደር እና ከመሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ያፈልጋል፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የግንባታ ፕሮጀክት አስተዳደር ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የሆነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እያስገነባቸው ከሚገኙ 11 በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ የኤምባሲዎች ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ፣ ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸው እንዲሁም ተቋራጩ ክስ የመሰረተበት እንዳሉ በሰነድ ተረጋግጧል፡፡

- በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ (ለምሳሌ 4.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚገመት የዋሽንግተን የጽ/ቤት፣ የአምባሳደር መኖሪያ ቤት እና የቀድሞ ጽ/ቤት ህንፃ ሙሉ ዕድሳት ስራ ፕሮጀክት በ2013 በጀት ዓመት ላይ የመጨረሻ ደረጃ ርክክብ መደረግ የነበረበት ቢሆንም ይህ መረጃ እስከተሰበሰበበት ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ርክክብ አልተደረገም)
- ተጨማሪ የስራ ትእዛዝ የተሰጠባቸው (ሶስት ፕሮጀክቶች፡- የለንደን ፕሮጀክት 434 ሺህ በላይ የእንግሊዝ ፓውንድ፣ የቻይና ፕሮጀክት 5.3 ሚሊዮን በላይ የቻይና የን እንዲሁም የጅቡቲ ፕሮጀክት 46 ሚሊዮን በላይ የጅቡቲ ፍራንክ)፣
- ተቋራጩ ክስ የመሰረተበት (የቱርክ ፕሮጀክት 16.4 ሚሊዮን የቱርክ ሊሬ)፣

በአንፃሩ የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት national democratic institute (NDI) ከሚባል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ጥናት ለማድረግና የተቋሙን አቅም ለመገንባት ጀምሮ የነበረው ፕሮጀክት በወቅቱ የተጠናቀቀ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ግን በኢንስቲትዩቱ የፕሮጀክት አሰራርን በተመለከተ የሂሳብ ክፍያ አፈፃፀም እና የፕሮጀክት ስራ አሰራር ግልፅነት ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያለመጠናቀቅ (ይህም ለተጨማሪ ከፍተኛ ወጪ መዳረግ) ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መጓተት፣ በአሰሪና ተቋራጭ መካከል ቅንጅት ማነስ፣ በአጠቃላይ ከፕሮጀክቶች አስተዳደር የክትትልና ቁጥጥር መላላት ሊመነጭ የሚችል አሳሳቢ ክፍተት ነው፡፡ በተጨማሪም የፕሮጀክቶች የሂሳብ እንቅስቃሴን የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት አለመኖር የፕሮጀክት አሰራር ግልፅነትን ጥያቄ ውስጥ የሚከት የሙስና ስጋት ነው፡፡
- ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የሚሰጥበት አሰራር (Variation work order) ምናልባት ቀድሞ የፕሮጀክቱን ዕቅድ በተገቢው መንገድ ከመገምገምና የሚሰሩ ስራዎች አስቀድመው እንዲካተቱ ከማድረግ አንፃር ክፍተት እንዳለ ጠቋሚ ሊሆን ይችላል (በአገሪቱ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ላይ በተከሰተ ለውጥ ምክንያት የመመጣት እድሉ እንደተጠበቀ ሆኖ)፡፡

4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በዘረጉ ተቋማት ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮችና ሙስና በእጅጉ እንደሚቀንስ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ተቋማት ህጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ በየጊዜው በውስጥም ሆነ በውጭ ኦዲተር የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሠራራቸውን የማስገምገም ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሠረት በዘርፉ ሥር በሚገኙ ተቋማት የኦዲት አስተዳደር ስርአት በጥናቱ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

በዘርፉ ያሉ ሁሉም ተቋማት በየሩብ ዓመቱ የውስጥ ኦዲት ስራ እየሰሩ መሆናቸዉን ከሪፖርቶች መገንዘብ ይቻላል፡፡ አብዛኞቹ የተቋማት አመራሮች የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ የማካሄድ ልምድ ያላችው መሆኑም ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በኦዲት ሪፖርት ግኝቶች መሰረት የተደረጉ ማሻሻዎችን በተመለከተ የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ማሻሻያዎችን ማድረጉን መረጃዎች ያመለከቱ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ሁለት ተቋማት ግን ይህ ስለመደረጉ ሰነድ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የኦዲት ሪፖርት ተደራሽነትን በተመለከተ በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሁሉም ተቋማት ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተደራሽ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ለሌሎች የስራ ክፍሎች ግን ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር ወይም ልምድ ስለመኖሩ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም፡፡

በአብዛኞቹ ተቋማት የሒሳብ አያያዝ ሥርዓትን ከማሻሻል አንፃር የፋይናንስ መረጃ አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ ወደ ተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS - Integrated Financial Management Information System) ለማስገባት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ በውይይት ወቅት ቢገለፅም፣ ይህ አዲስ አሰራር በትክክል እየተተገበረ መሆኑን በግልፅ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

በ2014 በጀት ዓመት ከተካሄዱ የውጭና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በግኝት የተለዩ የአሠራር ክፍተቶች እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡-

- ዋና ኦዲተር በ2014 በጀት ዓመት በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ባደረገው ኦዲት፦ የአገልግሎት ብቸኛ አቅራቢ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ከብር ሁለት ሚሊዩን በላይ በቀጥታ ግዥ መፈፀሙ፣ በመንግስት ግዥ መመሪያ ለውስን ጨረታ ከተፈቀደው የብር መጠን በላይ በድምሩ ብር 3.89 ሚሊዮን ብር በላይ ግዥ መፈፀሙ፣ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስርዓት ላይ በወጪ መመዝገብ የሚገባው ከብር 1.14 ሚሊዩን በላይ በገቢ የተያዝበት እና በሂሳብ መደብ ተለይተው ከብር 2.6 ሚሊዩን ብር በላይ ያልተመዘገበበት ሁኔታ መኖሩ፣ ግዥ የተፈፀመባቸው ንብረቶች ገቢ ስለመደረጋቸው ማረጋገጫ ሳይቀርብ ብር 274,206.07 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣ ከብር 54.9 ሚሊዮን በላይ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ ያልተወራረደ መሆኑ ተገልጿል፡፡
- በ2014 በጀት ዓመት የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ባካሄደው የውስጥ ኦዲት፦ ስልጠና ባልተሰጠበት ሁኔታ ለስልጠና ማዕከል ብር 148,404 በወጪ ሂሳብ መመዝገቡን፣ አገልግሎት ከሰጠ ድርጅት መቀነስ የሚገባው ሁለት በመቶ ታክስ ብር 83,060.87 ሳይቀነስ ክፍያ መፈፀሙን፣ እንዲሁም ከሐምሌ 2013 እስከ ሰኔ 2014 ዓ.ም. ድረስ ወጪ ተደርገው በድምሩ ብር 5,652,316.07 ሳይወራረዱ የቀረ መሆኑን ገልጿል፡፡

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የአገልግሎት ብቸኛ አቅራቢ መሆናቸው ሳይረጋገጥ በከፍተኛ ወጪ የቀጥታ ግዥ መፈፀሙ እንዲሁም በመንግስት ግዥ መመሪያ ለውስን ጨረታ ከተፈቀደው የብር መጠን በላይ ግዥ መከናወኑ በዘርፉ ተቋማት ውስጥ አሳሳቢ የሆነ የቁጥጥር መላላትና የተጠያቂነት ስርአት አለመኖር አመላካች ናቸው፡፡
- በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት የኦዲት ግኝቶች ላይ በመመስረት የተወሰዱ ማሻሻያዎች ስለመኖራቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ የማሻሻያ እርምጃዎች አለመኖር የተከሰቱ ብልሹ አሰራሮች እንደገና ለተቋሙ ስጋት የመሆናቸውን አጋጣሚ ስለሚያሰፋ እንደ ትልቅ ክፍተት ሊወሰድ ይችላል፡፡
- በዘርፉ ተቋማት ከፍተኛ መጠን ያለው ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ የፋይናንስ መመሪያ ጥሰትን እንዲሁም የቁጥጥር ሥርዓት መላላትን አመላካች ሊሆን ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡
- በዘርፉ ተቋማት የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት በትክክል እየተተገበረ መሆኑን በግልፅ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይህ ሥርዓት የሒሳብ አያያዝ እና ምዝገባን ወቅታዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ በማደራጀት ጥልቅ (comprehensive)፣ አስተማማኝ እና ወቅታዊ የፋይናንስ መረጃዎችን ለዋና ኦዲተር፣ ለፓርላማ፣ ለምርመራና አቃቤ ህግ አካላት በማቅረብ የፋይናንስ ቁጥጥርን ውጤታማነት ለማጠናከር ካለው ፋይዳ አንፃር ተቋማቱ ትኩረት ሰጥተው ያልሰሩበት ጉዳይ መሆኑን ያሳያል፡፡

4.11. የተቋማት የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

በውጭ ጉዳይ ዘርፍ ስር በሚገኙ ተቋማት ለሙስና ስጋት የሆኑ አሰራሮችና ሂደቶች (processes) ከነደረጃቸው እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡-

ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳላቸው የተገለጹ አሠራሮች፡-

- የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የኮንትራት አስተዳደር፣
- ጥናትና ምርምር ፕሮጀክት ሥራዎች ላይ ከሚንቀሳቀሰው በአንፃራዊነት ከፍተኛ ገንዘብ አንፃር የአሠራር ግልጽነት መጉደል፣
- መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ የፕሮፎርማ፣ ውስን እና ቀጥታ ግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ከፍተኛ ገንዘብ የሚያወጡ ንብረቶች ግዥ መፈፀም፣
- ግልፅነት የሌለው እና በቂ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግበት የተሽከርካሪዎች የጥገና አገልግሎት እና የነዳጅ አጠቃቀም አሰራር ስርአት፣

መካከለኛ የሙስና ተጋላጭነት እንዳላቸው የተገለጹ አሠራሮች፥-

- ንብረቶችን በአግባቡ ካለመያዝና ካለመመዝገብ ጋር ተያይዞ የንብረት አስተዳደር አሰራር፣
- መመሪያን ያልተከተለ የተለያዩ አገልግሎቶች ክፍያ አፈፃፀም፣
- ሚዛናዊ የቁጥጥር ስርዓትን በሚያላላ መልኩ የተለያዩ የስራ መደቦችን በተደራቢነት በአንድ ሰው እንዲሰሩ ማድረግ፣

ክፍል አምስት፥- ምክረ-ሀሳቦች

በዚህ ውስን ዳሰሳና ትንተና ጥልቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ቢያስቸግርም የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፥-

- ተቋማቱ ጥናትና ምርምር ፕሮጀክት ሥራዎች ላይ የሚታየውን የአሠራር ግልጽነት መጉደል መርምረው መፍትሔ ሊሰጡ ይገባል።
- የዘርፉ ተቋማት የተሽከርካሪዎች የጥገና አገልግሎት እና የነዳጅ አጠቃቀም አሰራር ላይ ተገቢውን የክትትልና ቁጥጥር ስርአት መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል።
- ተቋማት ለሙስና ስጋት የሆኑትን ከዕቅድ ውጭ፣ በቀጥታ፣ በውስን ጨረታ እና በፕሮፎርማ የተከናወኑ ግዥዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ፣ እንዲሁም አስገዳጅ ሁኔታ ሲከሰት በግዥ መመሪያ መሰረት ብቻ ለማከናወን የግዥ ዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና ቁጥጥር ላይ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል።
- የተጠናከረ የኮንትራት አስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ፣ ተጨማሪ የስራ ትዕዛዝ የሚሰጥበትን አሰራር በመቀነስ፣ አስቀድሞ የፕሮጀክቶችን ዲዛይን በተገቢው በመገምገምና ከግንባታው ዓላማ አንፃር የሚሰሩ ስራዎች በአግባቡ የተካተቱ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ እንዲሁም የኮንትራት አስተዳደር አቅምን በማሳደግ የግንባታ ሂደት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር እንዳይጋለጥ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።
- ፕሮጀክቶች በውሉ መሰረት በጊዜያቸው አለመጠናቀቅ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ እንዲሁም የህዝብን ሃብት ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ በፕሮጀክት ውል፣ ሂደትና ርክክብ ላይ ጥብቅ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

- የፋይናንስ አሠራር ሂደትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ ፈጣንና ቀልጣፋ አሠራር እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር የዘርፉ ተቋማት ለተግባራዊነቱ አስፈላጊ ጥረቶችን ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር በጅምር ደረጃ ላይ የሚገኘውን የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት (IFMIS) ሙሉ ለሙሉ መተግበር ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የውጭ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች፣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች፣ በጀት፣ ዕቅድ አፈፃፀም እና መሰል ጉዳዮችን ለማህበረሰቡና ባለድርሻ አካላት በተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮች ተደራሽ በማድረግ የዘርፉ ተቋማት ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማስፈን ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በተገቢው የሰው ኃይል፣ በጀት እና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ማደራጀት፣ እንዲሁም ከሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተጨማሪ ሙስናን ለመከላከል የሚያግዙ እንደ ህግ ክፍል፣ የውስጥ ኦዲት፣ የለውጥ ስራ አመራር፣ ወዘተ በአግባቡ የሚደራጁበት እና ተቀናጅተው በጋራ መስራት የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ የበላይ አመራሮችም የስነምግባር መከታተያ ክፍል ስራዎችን በአግባቡ መደገፍ፣
- ተቋማት የሙስና ስጋት እና የደንበኛ እርካታ ጥናቶችን እንዲሁም የኦዲት ግኝቶችን መሰረት በማድረግ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን የመለየት እና የማሻሻያ እርምጃ የመውሰድ ተግባር ላይ ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ሃብት ማስመዝገብ የሚገባቸውን አመራርና ሰራተኞች ሙሉ ለሙሉ እንዲያስመዘግቡ ማድረግ፣
- የተለያዩ የስራ መደቦችን በተደራቢነት በአንድ ሰው እንዲሰሩ ማድረግ ሚዛናዊ የቁጥጥር ስርዓትን የሚያላላ በመሆኑ መፍትሔ ቢበጅለት፣
- ተደራሽ እና ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ ዘመናዊ የጥቆማ መስጫ አሰራር ስርአት መተግበር፣
- የትምህርትና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ በማከናወን ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ያለበቂ ዕውቀትና ችሎታ ተቋማቸውን በሚጎዳ ሁኔታ ተቀጥረው ከሚያገለግሉ ሰራተኞች የዘርፉን ተቋማት ማጥራት፣

ማጣቀሻ ፅሁፎች

1. International Monetary Fund, Fiscal Monitor: Curbing Corruption, April 2019.
2. Organised Crime and Corruption Reporting Project (OCCRP), December 2017.
3. Transparency International, Corruption as Statecraft: Using Corrupt Practices as Foreign Policy Tools, 2019.